## በሀገራችን የተከሰተውን የማርበርግ ቫይረስ በሽታ አስመልክቶ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ለሕክምና በመጡ ታማሚዎቸች ላይ በተደረገ ምርመራ የማርበርግ ቫይረስ በሽታ (Marburg Viral Disease) መከሰቱን ጤና ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ጋር በመሆን ሕዳር 03 ቀን 2018 ዓ/ም ባወጣዉ ወቅታዊ መግለጫ ማሳወቃችን ይታወቃል፡፡

ይህ በሽታ ለመጀመሪያ ጊዜ እ.ኤ.አ በ1967 በጀርመን አገር ማርበርግ ከተማ የተገኘ ሲሆን በአህጉራችን አፍሪካ በጋና 2022፣ በኢኳቶሪአል ጊኒ 2023 ታንዛኒያ 2023/25 እንዲሁም በሩዋንዳ 2024 በወረርሽኝ መልክ መከሰቱ ይታወቃል።

በሀገራችን የመጀመሪያው የማርበርግ ቫይረስ በሽታ ታማሚ ከተረጋገጠበት ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ህዳር 8/2018 ዓ/ም ድረስ በአጠቃላይ በበሽታው ለተጠረጠሩ 17 ሰዎች የላብራቶሪ ምርመራ የተደረገ ሲሆን 3ቱ የማርበርግ ቫይረስ እንደተገኘባቸው እና ህይወታቸው እንዳለፈ ተረጋግጧል። እስከአሁን 6 ሰዎች የማርበርግ ቫይረስ በሽታ ምልክቶች አሳይተው ሕይወታቸው ያለፈ ሲሆን  በሽታውን ምልክቶች ካሳዩ ሰዎች ጋር ንክኪ የነበራቸው 129 ሰዎች ራሳቸውን ለይተው ክትትል እየተደረገላቸው ይገኛል።

ወረርሽኙን በአጭር ጊዜ ለመቆጣጠር እና የህብረተሰባችንን ጤና ለመጠበቅ ጤና ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፣ ከክልል ጤና ቢሮዎች፣ ከክልል የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩቶች እንዲሁም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ደንገተኛ የህብረተሰብ ጤና  ክስተት ፈጣን ምላሽ ዕቅድ በማውጣት በየደረጃው በተቋቋሙ የድንገተኛ የሕብረተሰብ ጤና አደጋ ማስተባበሪያ ማዕከላት አማካኝነት ስራዎችን እየሰራን እንገኛለን። እንዲሁም ሁሉን አቀፍ ፈጣን ምላሽ ሰጪ ቡድን ወደ ቦታው በመላክ የማርበርግ በሽታ ቅኝትና ምላሽ ስራዎች በተቀናጀና በተጠናከረ መልኩ በትኩረት እየተሰራ ይገኛል፡፡

እንደሀገር በሽታውን ለመመርመር የሚያስችል የላቦራቶሪ አቅም በመገንባት በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ውስጥ በራስ አቅም ምርመራዎችን እያከናወንን ሲሆን ወደ ክልሎች ለማስፋፋት የባለሙያዎችን አቅም እያሳደግንና አስፈላጊ ግብዓቶችን እያሟላን እንገኛለን።

በሽታው በተከሰተባቸው አካባቢዎች የተደራጀ የለይቶ ማቆያ እና ማከሚያ ማዕከላት የተቋቋመ ሲሆን በሌሎች ክልሎች ደግሞ በሽታው ቢከሰት ለማከም የሚያስችል ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል። ለእነዚህም ተቋማት የሚያስፈልጉ የሕክምና ግብአቶችና የኢንፌክሽን መከላከያ ቁሳቁሶችን ለማሟላት ጥረት እየተደረገ ሲሆን ወደፊትም ዕጥረቶች እንዳያጋጥሙ ዝግጅቶች እያደረግን እንገኛለን።

ሕብረተሰባችን ስለበሽታው ያለውን ግንዛቤ እንዲያድግና ወረርሽኙን ለመከላለከል እና ለመቆጣጠር የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበርክት ለማድረግ የሚያስችሉ የሕብረተሰብ ጤና መልዕክቶችን በተለያዩ የመረጃ ማሰራጫ መንገዶች በሰፊው እየተላላፈ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም በሀገር ውስጥ እንዲሁም በጎረቤት ሀገራት መግቢያና መውጫዎች ላይ የቁጥጥር እና የልየታ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

የበሽታውን ስርጭት ለመግታት እና የሚያስከትለዉን የጤና፣ ስነልቦናዊ፣ የማህበራዊ፣ እና ኢኮኖሚያዊ ጫና ለመቀነስ የሚከተሉት ምክረ ሃሳቦችን አሁንም መተግበር እንዳለባቸው እናሳስባለን።

የበሽታው ምልክቶች ከፍተኛ ትኩሳት፣ ብርድ ማለትና ራስ ምታት፣የጡንቻ እና የጀርባ ህመም ፣ ማቅለሽለሽ፣ የሆድ ህመም እና ተቅማጥ ከአፍ፣ ከአፍንጫ ወይም ከቆዳ ስር ደም መፍሰስ፣ ደረት፣ ጀርባ እና ሆድ ላይ በጣም ጎልቶ የሚታይ ሽፍታ ናቸው

- የበሽታው ምልክቶች የሚያሳይ ማንኛውም ሰው በወቅቱ ወደ ህክምና ተቋማት መሄድና የላብራቶሪ ምርመራ ማድረግ፣
- በበሽታው ተጠርጥረው በለይቶ ማቆያ ማዕከላት እንዲገቡ በሚጠየቁበት ወቅት ትብብር በማድረግ የበሽታውን ስርጭት መከላከል እና የሕብረተሰቡን ደህንነት ማረጋገጥ፤
- ምልክት ከታየበት ማንኛዉም ሰዉ ጋር ንክኪ በሚኖርበት ጊዜ የመከላከያ ዘዴዎችን መጠቀም፣
- ሁልጊዜ እጅን በአግባቡ በውሃና በሳሙና መታጠብ ወይም በሳኒታይዘር ማጽዳት፣
- በበሽታው ተጠርጥረው ሕይወታቸው ያለፈ ሰዎችን የቀብር ስነ ስርዓት የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በጥንቃቄ ማከናወን።
- ከጤና ሚኒስቴር እና ከኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የሚተላለፉ መረጃዎችንና የጥንቃቄ መልዕክቶችን መከታተልና መተግበር።
- ማንኛውም ጤና ተቋም ለታካሚዎች ልየታ ልዩ ትኩርት በመስጠት የማርበርግ በሽታ (Marburg viral disease) መሰል በሽታ መለየት፣ ማከም እና በአፋጣኝ ሪፖርት ማድረግ ያስፈልጋል።

***የበሽታውን ምልክቶች የሚያሳይ ማንኛዉም ሰዉ በሚመለከቱበት ጊዜ በአቅራቢያ በሚገኝ የጤና ተቋም ሪፖርት ማድረግ ወይም በ 8335 እና 952 ነፃ የስልክ መስመሮች ጥቆማ መስጠት ያስፈልጋል።***

**ዶ/ር መቅደስ ዳባ**
**የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር**
**ህዳር 08/2018 ዓም**
**አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**